## ቅሬታ ከቀረበ በኋላ ያለው ሂደት ምንድን ነው?

ለሜትሮፖሊታን ፖሊስ መሥሪያ ቤት (MDP) ወይም ለፖሊስ ቅሬታዎች ቢሮ (OPC) ቅሬታ ማቅረብ ይቻላል። የሚከተለው ዝርዝራዊ መግለጫ የቅሬታ ምርመራ ሂደቱን ዝርዝር ያሳያል።

### የMPD የቅሬታ ሂደት

**ደረጃ 1** ቅሬታው ለMPD ይቀርባል

**ደረጃ 2** ቅሬታዎን የሚከታተለው የMPD ባለሥልጣን ጉዳይዎን እየመረመረ እንደሆነ ያስታውቅዎታል። አስፈላጊም ከሆነ ባለሥልጣኑ ተጨማሪ መረጃ ይጨምራል።

**ደረጃ 3** ቅሬታው ይመረመራል- ምስክሮች እና ቅሬታ የቀረበበት ባለሥልጣን ቃለመጠይቅ ይደረግላቸዋል። ባለሥልጣኑ የቅሬታ አቅራቢውን ስም እና የቀረበበትን የቅሬታ ዓይነት የማወቅ መብት አለው። ይሁን እንጂ ቅሬታ አቅራቢው ስሙ እንዳይጠቀስ ከጠየቀ MPD የቅሬታ አቅራቢውን ስም ይፋ አያደርግም።

**ደረጃ 4** ምርመራው አልቋል እና የሚከተለው ውሳኔ ተላልፎአል፡

የተራዘመ – ሰውየው ያቀረበው ድርጊት መፈጸሙን እና የባለሥልጣኑ ድርጊት አግባብነት የጐደለው መሆኑ ለመወሰን በሚያስችል በበቂ ማስረጃ ከተደገፈ

ያልተሟላ መረጃ – በቀረበው አግባብ የሌለው ድርጊት ክስ መወሰን የሚያስችል በቂ መረጃ አለመኖር

ነጻ መውጣት – የተባለው ድርጊት መፈጸሙን ግን ድርጊቱ የMPDን መመሪያዎች፣ የአሠራር ሂደት ወይም ሥልጠና የማይጥስ መሆኑ ሲረጋገጥ

ያልተደገፈ – ተፈጸመ ለተባለው ድርጊት በምርመራው ማረጋገጫ የሚሆን ምንም ዓይነት መረጃ ሳይገኝ ሲቀር

**ደረጃ 5** የምርመራው ውጤት ይነገርዎታል። በውሳኔው ካልተስማሙ ለፖሊስ ዋና አለቃ በሚከተለው አድራሻ ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ።

Chief of Police
Metropolitan Police Department
300 Indiana Avenue, NW, Room 5080
Washington, DC 20001

### የOPC አቤቱታ ማቅረቢያ ዘዴ

**ደረጃ 1** የተሞላ እና የተፈረመ ቅጽ ከደረሰው በኋላ OPC አቤቱታው በሥልጣኑ ሥር መሆኑን ለማረጋገጥ ምርመራ ያደርጋል።

**ደረጃ 2** አቤቱታው በOPC ሥልጣን ሥር ከሆነ አብዛኛዎቹ አቤቱታዎች ለOPC መርማሪዎች ይመደባሉ። OPC ቅሬታውን ወደ ድርድር ሊወስደው ይችላል። ይህም በቅሬታ አቅራቢው እና በተጠያቂው ባለሥልጣን መካከል በአካል በመቅረብ በሚስጥር የሚደረግ ስብሰባን ያካትታል። ይህ ስብሰባ የሚመራው ወገናዊ ባልሆነ እና ለዚሁ ጉዳይ በሰለጠነ እንዲሁም ሁለቱንም ወገኖች በአንድ ላይ በመስራት ለቀረበው ቅሬታ የጋራ ስምምነት ላይ እንዲደርሱ በሚያደርግ ሰው ነው።

ቅሬታው በOPC ሥልጣን ሥር ያልሆነ የMPD ባለሥልጣንን የሚመለከት ከሆነ OPC ቅሬታውን ለMPD ለምርመራ ያስተላልፋል።

**ደረጃ 3** በምርመራው ውጤት መሰረት OPC ቅሬታውን ሊሽረው ወይም ምርመራው የፖሊስ ጥፋት መፈጠሩን አሳማኝ ምክንያቶች ካሳየ ቅሬታው ውሳኔውን በጽሁፍ ለሚያስተላልፍ ወደ ግላዊ የቅሬታ መርማሪ ይተላለፋል።

**ደረጃ 4** OPC ለቅሬታ አቅራቢው እና ለተጠያቂው ባለሥልጣን ውሳኔውን ያስታውቃል። ቅሬታው ከቀጠለ ለፖሊሶች ዋና አለቃ የቅጣት እርምጃ እንዲወሰድ ይተላለፋል። ስለተወሰደው እርምጃ እናስታውቅዎታለን። መልስዎን ለፖሊሶች ዋና አለቃ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላሉ።

በMPD ፖሊሶች ላይ በሕዝብ የቀረበውን የመጥፎ ተግባር አሰራር ቅሬታ OPC ለመቀበል፣ ለመመርመር እና መፍትሄ ለመስጠት ሥልጣን አለው። የቅሬታ ማቅረቢያውን ቅጽ በአካል በመገኘት፣ በፖስታ በመላክ፣ በፋክስ (202)-727-9182 ወይም ፎርሞቹን በማንኛውም MPD ዲስትሪክት ጣቢያ መስጠት ይችላሉ።

*Revised June 2014*

# በሜትሮፖሊታን ፖሊስ ባለሥልጣኖች ላይ አቤቱታዎች ማቅረብ

## ቅሬታ የማቅርብ ሥራዓት




» የበለጠ ለማወቅ **mpdc.dc.gov** ይመልከቱ

የሜትሮፖሊታን ፖሊስ መሥሪያ ቤት (MPD) ጥራት ያለው ፕሮፌሽናል አገልግሎት ለሁሉም ለመስጠት ዝግጁ ነው። MPD የባህሪ መበላሸት ወይም ትክክል ያልሆነ ተግባር አባሎቹ ሲፈጽሙ ዝም ብሎ አያይም። የፖሊስ አባላት ማንኛውንም ትክክለኛ ያልሆነ አሰራር በእርሶ ላይ ከፈጸሙ ወይም በሌላ ሰው ላይ ሲፈጸሙ ካዩ እና ምስክር ከሆኑ የተፈጠረውን ሁኔታ ለMPD ወይም ለፖሊስ ቅሬታ ማቅረቢያ ቢሮ(OPC) እንዲያቀርቡ እናበረታታለን። ቅሬታዎን ለማቅረብ ብዙ የተመቻቹ ሁኔታዎች አሉሎት እነዚህም በአካል፣በስልክ፣በኢሜል ወይም በፋክስ ናቸው። ቅሬታዎች የሚጣሩባቸው እና የሚገመገሙባቸው ሁለት የተለያዩ አሰራሮች አሉ።

የፖሊስ የቅሬታ ማቅረቢያ ቢሮ

» የኮሎምቢያ ዲስትሪክት መንግሥት ኤጀንሲ ሲሆን ከMPD ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ራሱን የቻለ እና የራሱ ምርመራ ሠራተኞች ያሉት ነው።
» ትክክል ያልሆነ የፖሊስ ተግባር ቅሬታዎች ከMPD ውጭ በሌላ ኤጀንሲ እንዲመረመር ምርጫ ይሰጣል።
» የተባለው ድርጊት እና ወከባው በተፈጸመ በ50 ቀናት ውስጥ የቀረቡትን ቅሬታዎች የማጣራት ሥስልጣን አለው ይህም ተገቢ ያልሆነ ወይም ከፍተኛ ኃይል መጠቀም፣ የስድብ ቋንቋ ወይም ባህሪ፣ የማዋረድ፣ የመድሎ፣ ለMPD ቅሬታ ስላቀረቡ መበቀል፣ ወይም አስፈላጊ የሆነውን መለዮ አለመልበስ፣ ወይም ስማቸውን እና የመታወቂያ ቁጥራቸውን በሕዝብ ሲጠየቁ ለመናገር ፈቃደኛ የማይሆኑትን ያጠቃልላል።

የሜትሮፖሊታን የፖሊስ መሥሪያ ቤት፣

» በአባሎቹ ላይ የቀረቡትን ቅሬታዎች በMPD የውስጥ ጉዳይ ቢሮ (IAB) እና በሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች ይመረምራል።
» በማንኛውም ጊዜ የቀረቡትን ማንኛውንም ዓይነት ተገቢ ያለሆኑ ተግባሮችን በOPC ሊመረመሩ የሚችሉትን ጨምሮ ይመረምራል።
» የጠቋሚው ማንነት ያልተገለጠባቸውን ቅሬታዎችን ይመረምራል።



# የፖሊስ ቅሬታዎች ማቅረቢያ ቢሮ

የፖሊስ ቅሬታዎች ማቅረቢያ ቢሮ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት መንግሥት የተመሰረተው በሕዝብ የሚቀርቡ በMPD በፖሊሶች የሚፈጸሙ ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶች አቤቱታዎችን የሚገመግም ገለልተኛ እና አድልዎ የሌለበት መድረክ ለሕዝብ ለማቅረብ ነው። የፖሊስ ቅሬታዎች ማቅረቢያ ቢሮ ዓላማው በዲስትሪክቱ የፖሊስ ክፍል ከፍተኛ የሐቀኝነት፣ ሙያዊ እና ሀላፊነት የሞላበት አሰራር ለመገፋፋት ነው። በፖሊስ የሚፈጸሙ አቤቱታዎች በሚገባ እና በጥንቃቄ ከተመረመሩ አና ሙያ ባላቸው ሰራተኞች ክታዩ የሕዝብ አምነት ይጠናከራል። የፖሊስ ቅሬታዎች ማቅረቢያ ቢሮ በከንቲባው የተሾሙ እና በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ካውንስል የጸደቁ ሲሆኑ በፖሊስ ቅሬታዎች ቦርድ ቁጥጥር ስር ናቸው።

OPC በMPD ባልሥልጣኖች ላይ የሚቀርቡ የሚከተሉትን አቤቱታዎች ያስተናግዳል።

» ወከባ
» አላስፈላጊ ያልሆነ ወይም ከልክ ያለፈ ኃይል መጠቀም
» መሳደብ፣ ማዋረድ ወይም አሳፋሪ ቋንቋ መጠቀም
» በዘር፣ በቀለም፣ በኃይማኖት፣ በዜግነት፣ በፆታ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በገጽታ፣ በፆታ ዝንባሌ፣ በፆታ ልዩነት ወይም ምልክት፣ በቤተሰብ ሃላፊነት፣ በሰውነት ጉድለት፣ በትምህርት፣ በፖለቲካ ግንኙነት፣ በገቢ ምንጭ ወይም በመኖሪያ ወይም በስራ ቦታ አድሎ ማሳየት።
» ለOPC አቤቱታ በማቅረበ መበቀል
» አስፈላጊውን መታወቂያ አለማድረግ ወይም በህዝብ አካል ሲጠየቁ ስም እና የአርማ ቁጥር አለመስጠት

የአቤቱታ ቅፆች እና መረጃዎች በሚቀጥለው ማግኘት ይቻላል፣

» OPCን በOffice of Police Complaints 1400 I Street, NW, Suite 700 Washington, DC 20005 መጎብኘት
» OPCን በስልክ ቁጥር 202) 727-3838 መደወል
» በOPC የ24 ሰዓት ነጻ ስልክ መስመር በ(866) 588-0569 መደወል
» የOPC ድህረ ገጽ policecomplaints.dc.gov መጎብኘት
» በዲስትሪክቱ ወደሚገኙ ማንኛቸውም የMPD ጣቢያዎቸ መሄድ

የአቤቱታ ቅጾች በሚቀጥለው መላክ ይችላሉ

» በአካል በመሄድ ወይም በፖስታ ከላይ በተጠቀሰው አድራሻ
» በ(202) 727-9182 ፋክስ በማድረግ
» ቅጾችን ወደ ማንኛውም MPD ጣቢያ በመውሰድ

# የMPD የውስጥ ጉዳዮች ቢሮ

የውስጥ ጉዳዮች ቢሮ (IAB) በባለሥልጣኖች ላይ የሚቀርቡ የጥፋት አቤቱታዎች በትክክለኛው መንገድ መሠራታቸውን የሚያረጋግጥ የMPD የውስጥ ክፍል ነው።

IAB በማንኛውም ጊዜ ማንኛውንም ዓይነት የፖሊስ ጥፋት አቤቱታዎችን በOPC የሚመረመሩትን እና ሌሎችንም ተመሳሳይ አቤቱታዎችን ይመረምራል። አቤቱታዎችን በተለያዩ መንገዶቸ ማቅረብ ይቻላል።

» በ IAB ወይም በማንኛውም የMPD ህንጻ በአካል በመሄድ
» ቅሬታውን በዝርዝር የሚገልጽ ደብዳቤ ለIAB ወይም ለማንኛውም የፖሊስ መሥሪያ ቤት በፖስታ መላክ
» ቅሬታውን ለውስጥ ጉዳዮች ቢሮ: በ(202) 727-4385, TTY: (202) 898-1454
የ24-ሰዓት መስመር: 1-800-298-4006 ማመልከት
» ቅሬታውን ለIAB በ(202) 727-5116 ወይም በፋክስ መላክ
» አቤቱታውን በኢሜል- citizen.complaints@dc.gov መላክ

የውስጥ ጉዳዮች ቢሮ
#6 DC Village Lane, SW, Building 1-A
Washington, DC 20032
(202) 727-4385

## አቤቱታ ሲያቀርቡ መታወስ ያለባቸው ነገሮች

ቀኑ፣ ዓመተ ምህረቱ፣ ሰዓቱ እና ቦታው

» የባለሥልጣኑ ስም፣ የመታወቂያ ቁጥሩ እና መግለጫው
» የምስክሮች ስም፣ አድራሻ እና የስልክ ቁጥሮች
» በአደጋው ጊዜ የነበሩ የመኪናዎች ታርጋ ቁጥሮች
» ጠቃሚ ናቸው ብለው የሚያስቡት ሌሎች ማስረጃዎች፣ እንደ ትራፊክ ትኬት፣ የፖሊስ ሪፖርት፣ ፎቶግራፎች እና የህክምና ማስረጃ ግልባጮች። ጉዳት ከደረሰብዎት የጉዳቱን ዓይነት እና መጠን
» ፎቶግራፎች እንዲነሱ እና የህክምና መረጃዎች ለማግኘት ቅሬታዎን ወዲያውኑ ማቅረቡ በጣም አስፈላጊ ነው።

ማንኛውም ቅሬታውን ለOPC ማቅርብ የሚፈልግ ሰው የተሟላ እና የተፈረመበት ፎርም አደጋው በተፈጸመ በ90 ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል። ቅሬታዎን ለMPD በማንኛውም ጊዜ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ።